# መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተጫነውን የኑሮ ውድነት ሸክም የሚያቃልል ተጨባጭ እርምጃ ባስቸኳይ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡

ከኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) የተሰጠ መግለጫ

ኢዴፓ በአገራችን የዋጋ ግሽበት አሳሳቢ ኢኮኖሚያዊ ችግር መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መንግስት በህዝቡ እለታዊ ህይወትና ኑሮ ላይ እየተከሰቱ ያሉ ከባድ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ተጨባጭ እርምጃዎችን እንዲወስድ ከማሳሰብ አልፎ የተለያዩ አማራጮችን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ኢህአዴግ በአንድ በኩል በኢዴፓ የቀረበውን አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች በጅምላ ሲያጣጥል የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ካቀረብናቸው አማራጮች አንዳንዶቹን የራሱ አስመስሎና ከራሱ ሀሳብ ጋር አቀላቅሎ ባልተሟላ ሁኔታ ለመተግበር ቢሞክርም የችግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆነውንና በሶሻሊስት አስተሳሰብ የተቃኘውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖሊሲ አቅጣጫ ስህተትነት ተቀብሎና አምኖ ሊያስተከክለው ባለመቻሉ ምክንያት በየጊዜው የወሰዳቸው እርምጃዎች ሁሉ ውጤት አልባ እየሆኑ የኑሮ ውድነቱና እየተባባሰ የመጣው ኢኮኖሚያዊ ችግሩ መፍትሄ አጥቶ ቀጥሏል፡፡

በቅርቡ መንግስት ችግሩን በዋጋ ተመን ቁጥጥር እፈታለሁ በሚል እርምጃ መውሰድ ከጀመረ ወዲህ የሸቀጦች ዋጋ ከጣሪያ በላይ በብዙ እጥፍ ከመጨመሩም በላይ የኑሮ ውድነቱ ፈጽሞ የማይታሰብ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ቀውሱ ላለፉት 5 ዓመታት ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደና እየተባባሰ የመጣ ቢሆንም ላለፉት ሦስት ዓመታት አንዴ እየዳከ ሌላ ጊዜ በፈጣን እርምጃ እየተጓዘ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሩጫ እየተምዘገዘገ ከ - እስከ ሳይባል የሸማቹን ማህበረሰብ ህልውና አሽመድምዶታል፡፡ ዛሬ የአብዛኛው ህዝብ ገቢ ለኑሮው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ሸቀጦችን መግዛት ጨርሶ ወደማይችልበት ደረጃ አሽቆልቁሏል፡፡ ገንዘብ ያላቸው ጥቂት ወገኖችም በገንዘባቸው መግዛት የሚፈልጉትን ሸቀጦች በገበያዉ ዉስጥ ፈልገዉ ማግኘት እያቃታቸዉ ነው፡፡ የትራንስፖርት አቅርቦቱም ወላጆች ከቤታቸው ወጥተው ቢሯቸው ሰርተው እንዲመለሱና ልጆቻቸዉም ወደ ት/ቤት ሄደው ለመምጣት የማያስችላቸው ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎችን በአብዛኛው ከውጭ አገር አቅራቢዎች የምትሸምት ሀገር ናት፡፡ ዓለም ላይ የተፈጠረው የአቅርቦት እጥረት ባስከተለው የዋጋ ንረት ምክንያት የምናስመጣቸው ሸቀጣ ሸቀጦች በመወደዳቸዉ ሊከሰት የሚችለውን አንፃራዊ ግሽበት መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በሀገር ውስጥ የሚመረቱና አቅርቦታቸው ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የሚሸፈኑ ሸቀጦችና የፍጆታ እቃዎች ዋጋ ውሎ ባደረ ቁጥር እጅግ አስደንጋጭ በሆነ ፍጥነት የመጨመራቸው ሁኔታ መንግስት ኢኮኖሚዉን ከሚመራበት አግባብና ከፓሊሲዎቹ ስህተት የሚመነጭ በመሆኑ ሃላፊነትን ከተቀበለው መንግስትና ከገዢው ፓርቲ የፖሊሲ አቅጣጫና የአመራር ድክመት መገለጫ ከመሆን አያልፍም፡፡

እንደሚታወቀው በየትኛውም አገር የመንግስት ዋነኛ ተዕልኮ የህዝብን የዕለት ከዕለት ሰላም በማስጠበቅ አቅም በፈቀደው መጠን የዜጎች ፍላጎት እንዲሟላ መጣር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ከመንግስት የሚጠበቁ ተግባራት ሰላም እንዲሰፍን ፍትህ እንዲረጋገጥ መልከም አስተዳደር እንዲኖር ከማድረግ ጀምሮ የሰዎች ሰርቶ የመብላትና የመኖር እድሎችን ማመቻቸትና መሰረታዊ መብቶችንና ጥቅሞቻቸው ሲናጉ መፍትሔ መስጠትን ያካትታል፡፡ ይህን መሰረታዊ ተልኮን ከማከናወን አንፃር ሲመዘን የኢህአዴግ መንግስት ሀገሪቱን ወደፊት ማራመድ ይቅርና ወቅታዊ ችግሮችን መፍታት እያቃተው ይገኛል፡፡

አሁን የተከሰተውን ከፍተኛ ያቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን አስቀድሞ የተረዳው ኢዴፓ ተገቢው የመፍትሄ እርምጃ እየተወሰደና የንግዱ እንቅስቃሴም አግባብ በሆነ ህግና ስርአት እየተመራ እንዲያድግ ማድረግ እንደሚቻል ደጋግሞ አሳስቧል፡፡ ይህን ማድረግ አለመቻሉም ኢኮኖሚያዊ አመራር መስጠት ከሚጠበቅበት አንድ መንግስት መደበኛ ተግባራት አንፃር ሲታዩ ከባድ ስራ ሊባል የሚችልም አይደለም፤አልነበረምም፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ በአንድ በኩል ለፖለቲካዊ ጥቅሙና ለስልጣኑ ህልውና አስፈላጊ በሆኑ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ከመጠን በላይ እየሰራ በሌላ በኩል ከህብረተሰቡ የእለት ተዕለት ህይወትና ኑሮ አንፃር እጅግ አስፈላጊ በሆኑ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ መስራት የሚገባውን ሥራ ጨርሶ በመተዉ ምክንያት አሁን የሚታየው ኢኮኖሚያዊ ችግርና የግብይይት ስርዓት መፋለስ ብሎም ማህበራዊ ቀውስ እየተባባሰ ሊመጣ ችሏል፡፡ የህዝብ ስልጣን በአግባቡ የሚረጋገጥበትን አሰራርና የመንግስት ተጠያቂነት የሚታወቅበት ስርአት ቢኖር ኖሮ አሁን ለተከሰተው ችግርና በህዝቡ ላይ እየደረሰ ላለው ጉዳት ኢህአዴግ ተጠያቂ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡

መንግስት ለዋጋ ንረቱ መነሻ ምክያቶቹ ከአቅርቦት እጥረት በተጨማሪ ጥቂት አቅራቢዎችና የሸቀጣ ሸቀጥ አስመጪዎች አምራቾች አከፋፋይና ቸርቻሪ በመሆን ገበያውን እንደፈለጉ ለመቆጣጠር በመቻላቸው እንደሆነ ለማስረዳት ሲሞክር ቆይተል፡፡ እነኝህ ጥቂት ወገኖች በዚህ ዓይነት ድርጊት ውሰጥ ተሰማርተው ያልተገባ ጉልበትና ስልጣን ተጠቅመው በብዙሀን ህይወትና ኑሮ ላይ ይህን ያህል ከባድ ችግር ሲፈጥሩ መንግስት መፍትሔ ለመስጠት ለምን ዘገየ የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ኢህአዴግ ማንኛቸውንም ከፖሊሲው ውድቀትና ከአመራሩ ድክመት የሚመነጩ ችግሮቹን ተከትሎ ለሚመጣ የህዝብ አስተያየትና ግፊት አነስተኛ ግምት በመስጠት ማንኛውንም ጥያቄ በህግ አግባብና ማህበረሰቡን አሳታፊ በሆነ መንገድ ከመፍታት ይልቅ በማስፈራራት፣ በጫናና በወከባ ለመፍታት ስለሚሞክር በዚህ አካሄዱ መነሻነት ለአስፈፃሚዎች የሚሰጠው ከልክ ያለፈ ስልጣን ከህግ በላይ እንዲሆኑና ለሰሯቸው ስህተቶች የማይጠየቁ፣ ለህዝብ ፍላጎትና መብት ደንታ የሌላቸው በሙስና የተዘፈቁ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ አንዳንድ በንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ግለሰቦችም በአገሪቱ የሰፈነው የመልከም አስተዳደር እጦት የህግ አለመከበርንና የስርአት መላላትን እንደመልከም አጋጣሚ በመጠቀም የፍጆታ እቃዎችን አቅርቦት ሙሉ በመሉ በራሳቸው ቁጥጥር ሥር በማድረግ የግብይይት ስርዓቱ ከነፃ ገበያ ውድድር መርህና መንፈስ ይልቅ በአድማ መንፈስና ስሜት በጓሮ በር እንዲወስኑ እድል ሰጥቷቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ኢህአዴግ ካለፉት አምስትና ስድስት አመታት ወዲህ እየተወሳሰበ መጥቶ እዚህ የደረሰውን ኢኮኖሚያዊ ቀውሰና የኑሮ ውድነት መንስኤው በተመዘገበው ኢኮኖሚያዊ እድገት ምክንያት እንደሆነና መፍታት

የሚቻለውም እድገቱን በማፋጠን ብቻ ነው ሲል እንደቆየ የሚታወቅ ነው። ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታም ለመረዳት የሚቻለው ግን ተመዘገቡ የተባሉት እድገቶች ምንጩ ከጤናማ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ የሚነሱ ባለመሆኑ ምክንያት ከዕለት ወደ ዕለት ስር እየሰደዱና እየተወሳሰቡ የመጡትን ኢኮኖሚያው ችግሩች እየፈታ ሳይሆን ይበልጥ እያወሳሰበ የሚገኝ መሆኑን ነው።

በኢህአዴግ በኩል አቅርቦትን ከፍላጎት ጋር በማመጣጠን ችግሩን ለመፍታት ይቻላል ሲባል የቆየ ቢሆንም በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት ባጭር ጊዜ ሊመጣጠን የማይችል እንደሆነ ቀጥሏል። ኢህአዴግ የተከተለው መንገድ አንዱ ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግና ሌላኛውን በመርሳት የአንዱ ኢኮኖማያዊ ዘርፍ እድገት የሌላኛውን የኢኮኖማያዊ ዘርፍ እድገት የሚያዛባ እየሆነ ባንድ በኩል እድገት ታየ ሲባል በሌላው በኩል ማሽቆልቆሉ እየሰፋ ኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ እንዲናጋ ሆኗል። መንግስት ይህንን ከባድ ችግር ፖሊሲውን በማረምና በማስተከከል ሊፈታው ሲገባ ትርጉም አልባ የሆኑ የቁጥጥር አሰራሮችን በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ ከድጡ ወደማጡ በሆነ መልኩ አየተጓዘ ይገኛል።

የችግሩ ሁሉ ምንጭ የገገርው ፓርቲ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ነው። ለዚህ ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው ከአንድ መደብ ጥቅም ጋር በተሳሰረ ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ለአንድ መደብ ወይም የኢኮኖሚ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የነጻ ገበያ ስርዓት ውድድርን በማዳከም አቅርቦት በተፈለገው መጠን እንዳያድግና ከህዝቡ ፍላጎት ጋር በአንፃራዊነት መጣጣም እንደሚችል መደረጉ ሲሆን በሌላ በኩል ኢኮኖሚው ከሚፈቅደውና መሸከም ከሚችለው በላይ ግሽበትን እጅግ በሚያባብስ መልኩ በዘመቻ ትላልቅ የመሰረተ ልማት መስኮች ላይ መዋለ ነዋይ ያለገደብ ማፍሰሱ ነው። ኢህአዴግ ይህንን ያልተመጣጠን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲያርም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ሁሉ እድገቱ እንዳይመጣ ከመፈለግ የሚመነጭ አድርጎ ሲያጥላላ ቆይቷል።

ኢዴፓ የሰፋፊ መሰረተ ልማት ግንባታዎች መስፋፋትንና በዚህ ምክንያት የሚታየውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ቢቀበልም ይህ ኢኮኖሚያዊ እድገት ብቻውን የፖሊሲ ትክክለኛነትንና ያመራር ስኬትን ማሳያ ሊሆን እንደማይችል በጽኑ ያምናል። የኢኮኖሚ አመራር የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጭው በሚል ዘይቤ የሚመራ ሳይሆን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን በማገናዘብና በማመጣጠን የዜጎችን ኑሮ በማያናጋ መንገድ የሚከናወን መሆን አለበት። በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ ለሚካሄደው መሰረተ ልማት ግንባታ ለሚውለው መዋለ ንዋይ ፍሰት ምክንያት በተፈጠረው አንጻራዊ የመግዛት አቅም ማደግና በተቃራኒው ባለበት በሚድህው አቅርቦት ምክንያት የተቀሰቀሰው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ህብረተሰቡን እጅግ ከባድ ዋጋ እያስከፈለው ይገኛል የተፈጠረው የዋጋ ግሽበት በህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወቱ ላይ እየፈጠረ ያለው ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ቀውስ የኢህአዴግ መንግስት የኢኮኖሚ እድገት ትንበያን ትርጉም በሚያሳጣ መልኩ ጥያቄ ላይ ጥሎታል። ያልተመጣጠነው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታም እያስከተለ ያለው ያልተስተካከለ የገቢና የኑሮ ልዩነትም እንዲሁ ከልክ በላይ እያሻቀበ ይገኛል። ይህ ባገሪቱ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ላይ አደጋ የሚደቅን መሆኑም ግልጽ ነው።

በኢዴፓ በኩል በአንጻራዊነት ከወቅታዊና አስፈላጊነት እንዲሁም ኢኮኖሚው ሊሸከም ከሚችለው አቅም አንጻር የተፈተሹ የመሰረተ ልማት ግባታዎችን ማካሄድና ለዚህም የሚያስፈልገውን መዋለ ንዋይ የማፍሰስ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ሆኖ አያውቅም፡፡ ነገር ግን ይህ ወጪ ኢኮኖሚው ከሚሸከመው በላይ መሆኑ የሚያስከትለውን ከፍተኛ የግሽበት ችግር በማመዛዘን መንግስት የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን የህዝቡን እለታዊ ኑሮ በማያናጉበትና ማህበራዊ ቀውስን በማያስከትሉበት መንገድ እንዲከናወኑ ማድረግ ይገባል፡፡

ኢህአዴግ በታሪክ ለመጀመር ጊዜ የእድገት እንቅስቃሴን አመጣሁ ማለትን ከኢኮኖሚያዊ ምክንያትነቱ በላይ ለፖለቲካዊ ውድቀት መሸፈኛነት ከልክ በላይ ስለሚፈልገው ያስመዘገበው ኢኮኖሚ የእድገት እንቅስቃሴ እያስከተለ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ቀውሰና በዋጋ ግሽበት ምክያት ህብረተሰቡን ከልክ በላይ ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን ለማየትና ለመቀበል እየቻለ አይደለም፡፡ አመጣሁ የሚለውም እድገት እንቅስቃሴ ህዝብ በልቶ ለማደር ያለውን ፍትሐዊ ጥያቄ መልስ ሰጭ ከመሆን ይልቅ ለኢኮኖሚያዊው አለመረጋጋት፣ ለኑሮ ወድነት እና ተጓዳኝ ለሆኑ ማህበራዊ ቀወሶች ምንጭ እየሆነ ነዉ፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው በኢዴፓ አማራጭ ፖሊሲ መሰረት የመሰረተ ልማት ግንባታ ሳይቋረጥ በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ግሽበት በአንጻራዊነት ለመቆጣጠር ወይም ከቁጥጥር ሳይወጣ እንዲቀጥል ለማድረግ ይቻላል ብሎ ያምናል፡፡ አሁን በሀገሪቱ ውስጥ እየታየ ያለው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ወደዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት በገጠርና ከተማ ልማት በእርሻና በኢንዱስትሪው እድገት ላይ ተመጣጠኝና ተደጋጋፊ በሆነ ትስስር ላይ በማተኮር በከተማ የሚደረገው ኢንቨስትመንት ለገጠር ልማት በሚፈጥረው አመቺነት ተጠቅሞ የገጠር ኢኮኖሚ እንዲያድግ የግብርና ዘርፍ በሰፋፊና በሜካናይዝድ እርሻ አማካኝነት የሚፈጠረውን ምርት ኢንዱስትሪው እንዲቀበለው በማድረግ አርሶ አደሩ በገበያ እጦት እንዳይጠቃና ከገበያ እንደይወጣ በማድረግ ገበያው የሚጠይቀውን የኢንዱስትሪና የሰብል ምርት አቅርቦት በአንጻራዊነት ማሻሻል ይቻላል፡፡ ዛሬ ለውጭ ባለ ሀብቶች በከፍተኛ መጠን እየተሸነሸነ የሚሰጠው መሬት ቀደም ሲል ለሀገር በቀል አልሚዎች በተወሰነ ደረጃ ድጋፍ እየተደረገላቸው እንዲያለሙ ቢመቻች ኖሮ ያሁኑ የምግብ ሰብል እጥረት ችግር ይህን ያህል ከባድ ከመሆኑ በፊት ቀስ በቀስ እየተቀረፈ ሊመጣ ይቻል ነበር፡፡

ነገር ግን ኢህአዴግ እርሻ ካላደገ ኢንዱስትሪ አያድግም በሚል ፈሊጥ እርሻን ማእከል አድርጎ ለሩብ ምዕተ አመታት የተከተለው ፖሊሲ ገጠሩንም በሚፈለገው ደረጃ ሳያለማ ከተማውንም ሳያሳድግ ግብርናውም ከእጅ ወደ አፍ ከመሆን እንዳይዘል ኢንዱስትሪውም ባለበት እንዲቀር ይህንንም ተከትሎ የኢኮኖሚ መናጋት፣ እንዲከሰትና ግሽበት እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል፡፡

ኢህአዴግ በተለያዩ ግፊቶች ተገዶ ያደረጋቸውን ማሻሻያዎች ቀደም ሲል ኢዴፓ ሲያቀርብ በነበረው መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ተችሎ ቢሆን ኖሮ ያገራችን የኢኮኖሚ እድገት ቀስ በቀስ በተመጣጠነ ሁኔታ እየጎለበተ መጥቶ አሁን የሚታየው አይነት ችግር አይከሰትም ነበር፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ ብዙ ጊዜ አባክኖ ያለውጤት ከተጓዘ በኋላ አሁን ሁሉንም ነገር ባንድ ጊዜ ለማስፈጸም እያደረገ ያለው ሙከራ አንዱን ከልክ በላይ በመወጠር ሌላውን ከልክ በላይ ጎዶሎ እያደረገው ነው፡፡

ለበርካታ ምዕተ ዓመታት የተከማቹ የመሰረተ ልማት ችግሮችን በሁለትና ሶስት ዓመታት ለመፍታት የሚያደረገው ርብርብ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ አቅም እና የህዝቡን ችሎታ  ያላገናዘበ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል የሌለው ለከባድ ሙስና በር የሚከፍት ዘመናዊና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ወቅታዊነቱና አስፈላጊነቱ እየተፈተሸ የማይተገበር ከመሆኑ በተጨማሪ እነዚህን የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ለማስፈጸም የሚፈሰው መዋለ ንዋይ ግሽበትን እጅግ የሚያባብስ ነው። በተጓዳኝም እጅግ በተፋጠነ ሁኔታ ለትላልቅ ግንባታዎች የሚወጣው በብዙ በቢሊዮን የሚቆጠር መዋለ ንዋይ  ብቸኛ አንቀሳቃሽ ለሆኑ ጥቂት ግለሰቦች ብቻ በር የከፈተ በመሆኑ በኢኮኖሚው ውስጥ በተመጣጣኝ አቅርቦት ያልተደገፈ አዲስ የመግዛት አቅም በመፍጠሩ የኢኮኖሚው ሞተር ዋነኛ ዘዋሪ ሆነው ብቸኛ ዋጋ ተማኝ፣ አምራችና አካፋፋይ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ ገበያው የጥቂቶች ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል ። ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግስት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ስራውን የማከናወን ልምዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረና እየላላ ከመምጣቱም በላይ ግብር የመሰብሰብ አቅሙ መጠናከርን ተከትሎ በፈጠረው አቅም ልክ ወደ ኢኮኖሚው የሚያስገባው መዋለ ንዋይ ከምርታማነትና ምርት አቅርቦት ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ የዜጎችን የመግዛት አቅም እያዳከመ ግሽበቱን ከልክ በላይ አባብሶታል።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ዛሬ ላይ እጅግ ተባብሶ የሚገኘውን የኢኮኖሚ ቀውስና የኑሮ ውድነት ችግር ለማስወገድ በመንግስት በኩል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ችግር ያለባቸውና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጽንሰ ሐሳቦችን በመፈተሽና ዘላቂ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በመቀየስ  ላይ የተመሰረቱ መሆን ሲገባቸው ጥልቀት በጎደላቸውና ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ ብቻ ሳይሆን ችግሩን በይበልጥ የሚያባብሱ መንገዶች መሆናቸው ተረጋግጧል። ከጥቂት ወራት በፊት የዋጋ ተመንና የቁጥጥር ስርዓት ሲታወጅ ኢዴፓ አምርሮ ላሰማው ተቃውሞ ኢህአዴግ የራሱን ፖለቲካዊ ትርጉም በመስጠት እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ቢያጥላላውም እርምጃው የወራትን  እድሜ ሳይስቆጥር የተሳሳተ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። መሰረታዊ የአቅርቦት እጥረት ባለባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች እያንዳንዱ ነጋዴ ሸቀጡን መንግስት በተመነው ዋጋ እንዲሸጥ ለማስገደድ አይቻልም። ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል የቁጥጥር ስርአትና ተቋምን ለመዘርጋት መሞከር የድመትና የአይጥ ጨዋታ  ከመሆን ሊዘል አይቻልም። መንግስት ተመን ያወጣላቸው ሸቀጦች ከጥቂት ወራት በኋላ  ከሶስትና ከአራት እጥፍ በላይ ዋጋ በመጨመሩም መንግስት ምንም ማድረግ አቅቶት በዝምታ ውስጥ መገኘቱም የዚህ ማረጋገጫ ነው።

አሁን ላለው ከፍተኛ የኢኮኖሚያዊ ቀውስ፣  የኑሮ ውድነት እና የገበያ ስርዓት መፋለስ ዓይነተኛ ችግር ምንጩ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ድክመት ነው። ይህ በሌላ በኩል የሚጠቁመው አጠቃላይ ችግሩ የፖሊሲ ችግር መሆኑን ነው። ችግሩም ለዘለቄው ሊፈታ የሚችለው የፖሊሲ ለወጥ በማድረግ ወይም ለተሻለው የፖሊሰ  አማራጭ መንገድ በመክፈት ብቻ ነው። የንግዱን እንቅስቃሴ ጥቂት ሰዎች ተቆጣጥረውት ለስርጭቱ መዛባት ምክንያት ሆነዋል ለሚባለውም ችግር ዋነኛው ተጠያቂ ኢህአዴግ ብቻ ነው። ይህ ሊከሰት የቻለው በመንግስት አስተዳደርና ሹመኞች ውስጥ ተጠያቂነት ባለመኖሩ ጭምር ነው። የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ባልሰፈነበት ሁኔታ ማንኛውንም አሰራር ውጤታማ ማድረግ አይቻልም። መልካም አስተዳደርና የፍትህ  እጦት በአጠቃላይ የዲሞክራሲ መጥፋት ያስከተለው ፖለቲካዊ ችግር ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተዳምረው በአገሪቱ ውስጥ የኢኮኖሚ እድገት አለ ሊባል አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ከባድ ለሆነ የኑሮ ውድነት ስቃይና ችግር

ሰለባ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ ቀውስ ከቀን ወደቀን ይቀንሳል ተብሎ ተስፋ ቢደረግም ችግሩ እየተስፋፋ ቀጥሏል ኢህአዴግ ችግሩን የመፍታት አቅም እያጣ መሆኑን በግልፅ እየታየ ይገኛል፡፡ ኢህአዴግ ተጨባጭ እርምጃ በመውሰድ ይህን ችግር ለመፍታት አለመቻሉ ኢዴፓን እጅግ አሳስቦታል፡፡

ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግም እንደ ድርጅትም ሆነ መንግስት በጥቅሉ አሁን ያለው የዋጋ ግሽበትና የግብይይት ስርዓት መዛባት የኢትዮጵያን ህዝብ እጅግ ለመራር ሰቆቃ እየዳረጉት መሆኑን ተረድተው እስከሁን ሲደረጉ ከነበሩት መፍትሄ አልባ ክርክሮችና እርምጃዎች በተለየ በኢዴፓ የቀረቡትን ከፍተኛ የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን በአፋጣኝ እንዲወሰድ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ በወቅታዊነት የተከሰቱትና እየተባባሱ በሚገኙ የአቅርቦትና የግብይይት ችግሮች ላይ ኢዴፓ ከዚህ ቀደም በመፍትሔነት ካቀረባቸው ውስጥ አሁንም ምላሽ ያላገኙትን ተግባራዊ እንዲደረጉ ጥሪውን አበክሮ ያቀርባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዋጋ ተመን በመጣልና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት መንግስት የወሰደው ጣልቃ ገብነት በግብይይት ስርዓቱና በአቅርቦት ላይ የፈጠረው መዛባት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ከዚህ አንጻር የተጣለውን የዋጋ ቁጥጥሩና የዋጋ ትመናው በማንሳት ግብይይቱ በነጻ ገበያ የውድድር ስርዓት እንዲመራ፣ ነጋዴው ማህበረሰብ አላግባብ የተነጠቀውን የአስመጭነት መብቱ ተመልሶለት አቅርቦቱን እንዲቀጥልና በመንግስት በኩል በተለይ አቅርቦትን በማሳደግና ጉድለትን በማሙላት እንዲሁም በትርምስ የተሞላውንና ለሙስና የተጋለጠውን የስርጭት ስርዐቱን በማረም በዝቅተኛ ኑሮ ላይ ለሚገኘው ማህበረሰብ ያለውጣ ውረድ ተደራሽነትን እንዲያረጋገጥ ኢዴፓ በድጋሚ ያሳስባል፡፡